DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ህዳር 4፣ 2021
ውድ የ Brightwood Elementary ትምህርት ቤት፣

ይህ ደብዳቤ ህዳር 1 ቀን በብራይውውድ ለመጨረሻ ጊዜ የተገኘው አንድ ግለሰብ እና በኖቬምበር 4 ላይ በብራይውዉድ የተገኘ አንድ ግለሰብ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) አወንታዊ ምርመራ እንዳደረጉ ለማሳወቅ ነው። ግለሰቦቹ ካምፓስ ውስጥ የሉም እና በህክምና እስኪፀዱ ድረስ አይመለሱም።

**በDCPS ንክኪ ያላቸውን መከታተያ ቡድን (Contact Tracing team)፣ በዲሲ ጤና፣ እና በ[ዲስትሪክቱ የCOVID-19 የጤና እና የደህንነት ጥበቃ መመሪያ]() በተወሰነው መሠረት፤ ተማሪዎ የምርመራ ውጤቱ በሽታው እንዳለው (positive) ከሆነው ግለሰብ ጋር የቅርብ ንክኪ (close contact) እንዳልነበረው ተለይቶ-ታውቋል፤ እና ምርመራ ማድረግ ወይም እራስን-አግልሎ መቆየት (self-quarantine) አያስፈልገውም።**

በሽታው ካለበት (positive ከሆነ) ግለሰብ ጋር የቅርብ ንክኪ (close contact) እንደነበረ የታወቁ ሰዎች፤ ወዲያውኑ እንዲያውቁት የተደረገ እና በዚህ ተጽዕኖ የደረሰባቸው ማንኛውም ተማሪዎች ተገልለው በሚቆዩበት (quarantine በሚያደርጉ) ጊዜ፣ እንዴት የትምህርት አሰጣጥን እንደሚያገኙን ጨምሮ፤ ቀጣይ-እርምጃዎችን የሚያስረዳ መመሪያዎች ይሰጣቸዋል።

ለእናንተ ግንዛቤ እንዲረዳ፤ የዲሲ ጤና፣ ከPK-12 ባለው አቀማመጥ ውስጥ - የቅርብ ንክኪ (close contact) የሚለው የሚተረጉመው፤ "ከተበከለው ሰው ጋር በ6-ጫማ ርቀት ለ15 ደቂቃዎች የነበረ ሰው፣ በ24-ሰዓት ጊዜው ውስጥ፤ ህመሙ ከመጀመሩ ሁለት ቀናት በፊት በቦታ የነበረ (ወይም ምልክት-ለማያሳዩ የተበከሉ ሰዎች/asymptomatic infected people፣ በሽታው እንዳለ (positive) የምርመራ ውጤታቸው ከተሰበሰበበት ሁለት ቀናት በፊት) የተበከለው ሰው እራሱን ለይቶ እስከሚቆይ ጊዜ-ድረስ ያለውን ነው።"

DCPS፣ [እንዱ-ከአንዱ ላይ የተደራረበ የቅነሳ እርምጃዎችን (layered mitigation measures)]() በትምህርት ቤታችን በቦታው በማስቀመጡ፤ በሽታው እንዳለ (positive) የምርመራ ውጤት ካላቸው ሌሎች ተማሪዎች፣ ከ 3 እስከ 6 ጫማ ርቀት ውስጥ የነበሩ ተማሪዎች፤ በተከታታይነት ወይም በትክክል በደንብ የሚሸፍን የፊት መሸፈኛ ማስኮችን (masks) ከነበራቸው፣ እንደ የቅርብ ንክኪ (close contact) ተብለው አይወሰዱም። በእነዚህ እርምጃዎች ምክንያት፤ አንዳንድ የክፍል-ውስጥ ጓደኞች፣ ተግልሎ ለመቆየት (quarantine ለማድረግ) ትዕዛዛቶቹን ላያገኙ ይችላሉ ማለት ነው። በተጨማሪም፣ በሽታው መኖሩ (positive case መኖሩ) በማሳወቂያው-ጊዜ፣ እና መጠነ ሰፊ ጥንቃቄ ለመውሰድ ሲባል፤ ክፍሎችን፣ የቢሮ አካባቢዎችን፣ የስብሰባ ክፍሎችን፣ እና ሌሎች የጋራ መጠቀሚያ ቦታዎችን ጨምሮ፤ ህንፃው የሚጸዳ እና ከብክለት ነፃ (disinfected) ይደረጋል።

**እራሳችንን፣ ቤተሰባችንን፣ እና የትምህርት ቤት ማህበረሰባችንን ከCOVID-19 በመከላከል ላይ፣ ሁላችንም ሚናችንን እንጫወታለን።** ይህን የCOVID-19 ስርጭትን ለመግታት እና ማህበረሰባችንን በደህንነት ለመጠበቅ፤ የየዕለቱ እርምጃዎችን ያካተተውን [Stronger & Safer Together Pledge]()ን፣ እንድትወስዱ የምናበረታታበት ምክንያቱም ይህ ነው።

- የክትባታቸው ሁኔታ ምንም-ሆነ ምን፤ ምልክቶች ከታዩ በኋላ የተወሰደላችሁን የCOVID-19 ምርመራ ውጤታችሁን የምትጠብቁ ከሆነ፤ በሽታው እንደሌለ (negative) የምርመራ ውጤታችሁን እስከምታገኙ ድረስ እባካችሁን በመኖሪያ ቤታችሁ ውስጥ ቆዩ።

- በሽታው እንዳለ (positive) የምርመራ ውጤት ካገኛችሁ፣ **ወይም** እነዚህ ምልክቶች ከገጠሟችሁ፤ እንደ ትኩሳት፣ ሣል፣ ወይም ትንፋሽ ማጠር — እባካችሁን በቤት ውስጥ መቆየት እና እራሳችሁን ከቤተሰባችሁ መለየት፣ ትምህርት ቤታችሁን ወዲያውኑ ማሳወቅ እና የጤና እንክብካቤ-ሰጪያችሁን አነጋግሩ።

- ተማሪዎቻችን እና ቤተሰቦቻችን፣ የCOVID-19 ክትባትን እንዲከተቡ በእጅጉ እናበረታታቸዋለሁ። ሂደቱን ለመጀመር እና በአካባቢያችሁ-ያለውን ነፃ የትምህርት ቤት ክሊኒክ ለማግኘት፤ vaccinate.dc.gov ጎብኙ።

ለማህበረሰባችን በጣም-ፈታኝ የሆነ ግዜ እንደሆነ እናውቃለን። ስለ ጤና እና የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎች እና ጠንካራ፣ የማይበገር፣ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ዓመት እንዲኖረን ለማገጋገጥ አብሮ በህብረት ስለመስራት፤ ያሉትን መረጃዎች ማቅረባችንን እንቀጥልበታለን።

እናመሰግናለን፣

Maurice Kennard
Principal, Brightwood Elementary